**ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል**
**21 ኛ ሳምንት**
**አስቴር - ክፍል ሁለት**

## ዓላማ

- የጸሎትና ጾምን ኃይልና እግዚአብሔር ለሁሉም ምክንያት እንዳለው መማር

## የሚጠና ጥቅስ

- ***"በርቱ ልባችሁም ይጽና።"*** መዝ.30 (1)

## ምንባብ

- መጽ. አስቴር 3-7

## መግቢያ

- አስቴር እንዴት ንግሥት እንደሆነች ታስታውሳላችሁ?
- በዛሬው ትምህርታችንም አስቴር እንደ ንግሥት ካላት ክብር ይልቅ ለሕዝቧ ማሰቡዋንና ምን እንደሠራችም እንማራለን።
- መርዶክዮስና ሐማ የሚሉ ስሞችን አስቡ።

## ትምህርቱ

- ንጉሡ አርጤክስስ መልከ መልካምዋን አስቴር ንግሥት አድርጎ ሾማት፤የእግዚአብሔር ሕዝብ አይሁዳዊት ነበረች።
- ሐማ የተባለ የንጉሡ ባለሥልጣንም ነበር። አይሁዳንን ለማጥፋት ክፋት አሰቦ÷ ንጉሡንም አሳስቶ በግዛቱ ያሉ አይሁድ በሙሉ የሚገደሉበት አዋጅ አስወጣ። አዋጁ ምንድነው?.......
- ንጉሡ አስቴር አይሁዳዊት መሆኗን አላወቀም። መርዶክዮስ /የአስቴር አጎት የሐማን ተንኮል ሲሠማ ወደ ንጉሡ ገብታ አዋጅን እንድታስቀይር ላከባት። አስቴርም ሕዝቡ በሙሉ ለ3ት ቀናት እንዲጾሙ ከዚያ በኋላ ግን ንጉሡን እንደምታናግረው ነገረቻቸው። አስቴርና ሕዝቡም ለሦስት ቀን ጾሙና ጸለዩ።
- ንጉሡ በወርቃማ ዘንጉ ምልክት ያልሠጠው ወይም ሲገባ ያልፈቀደለት ሰው ካልሆነ ማንም ንጉሡን ገብቶ ማናገር አይችልም ነበር። አስቴርም ንጉሡ አልጠራትም ማናገር ፈልጋ ነበርና በጣም ተጨነቀች። ከጾመችና ከጸለየችም በኋላ ንጉሡን ለማናገር ወስና  ጥሩ አለባበስ ለብሳም ወደ ንጉሡ ሄደች ምልክት ሠጥቶ እስኪጠራትም በቤተ መንግሥቱ ደጅ ትጠባበቅ ጀመር።
- ንጉሡም ተደስቶ አስቴር እንድትገባ በወርቃማ በትሩ ምልክት ሰጣት። አስቴርም ገብታ ንጉሡን ከሐማ ጋር የሁለት ቀን ድግስ አዘጋጅታ ጋበዘችው። በግብዣውም ጉዳይዋን ነገረችው። እስከ መንግስቱ እኩሌታ እንደሚሠጣት ቃል ገባላት። ሐማ ሕዝቡን ሊገድል እቅድ እንዳለውና አይሁድ ወገኖችዋ መሆናቸውን ነገረችው። ንጉሡም አይሁድ እንዳይጎዱና እንዳይገደሉ የሚል አዋጅ አወጣ። በክፉ እቅዱም ሐማ እንዲገደል ፈረደበት።

## ጥያቄዎች፡-

1. የእግዚያብሔር ሕዝብ ለመጉዳት ያቀደው ማነው?
2. መርዶክዮስ አስቴር ምን እንድታደርግ ነገራት?
3. አስቴር ንጉሡን ለማናገር ለምን ተጨነቀች
4. ንጉሡን ከማነገርዋ በፊት ምን አደረገች?
5. ሕዝቡ እንዲገደሉ አዋጅ ሲወጣ ሕዝቡና አስቴር ምን አደረጉ?
6. ከአስቴር ምን ተማራችሁ?
7. ሐማ ምን ሆነ?

**ይቆየን።**